በትሕትና ቃል ሲጠይቁት ያሳያል። ሰማያዊ ንጉሥ ክርስቶስ ግን ይኸን ሁሉ ለወንድሞቼ ለችግረኞቹ ያደረጋችሁት ስለኔ ስለኔ ለእኔ እንዳደረጋችሁት እቆጥርላችኋለሁ ሲል ተናግሯል። ማቴ 25፤31-40

## የጽድቅ ሥራ

**ጽድቅ ማለት፣**

- ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ስሜት ማግኘት ወይም መኖር ማለት ነው። የሥነ ምግባርን ሕግ ሁሉ ለመፈጸም ንፁሕና ፍፁም የሆነ ፍቅር እግዚአብሔር ያለው ሆኖ መገኘት ከፍቅሩ የተነሣ ፍቃዱን ለመፈጸም የሚያደርገው ጥረት።
- በሰይጣን ላይ መሰልጠን /ድል መንሳት/፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ለመውረስ ብቁ ሆኖ መገኘት፣ በእውነት ጎዳና መራመድ ምግባረ ሰናይ መፈጸም።
- በእግዚአብሔር ምሥጋና ጸንቶ መኖር ወዘተ የጽድቅን ቦታ ለመያዝ የጽድቅን ግብር የሆኑትን ሁሉ ለመፈጸም በግድ ያስፈልጋል።
- ባመኑት እምነት ጸንቶ መኖር።
- የጽድቅን ሥራ ለመሥራት በጎ ፈቃድ ያለው ሆኖ መገኘት
- የሚሠራውን የሚያምን፣ የሚያምነውን የሚሠራ ሆኖ መገኘት። ለጽድቅ የሚያበቃውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን ተግቶ በመሥራት ጽድቅ ይገኛል። ያዕ 2፤21-24 ሮሜ 2፤13

በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉም። ሮሜ 2፤13& ከአምላክና ከባልንጀራ ፍቅር የተነሳ መፈጸም አለበት። ማቴ 22፤37 የጽድቅ ሥራ በሁለት ከፍለን መመልከት እንችላለን።

### እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ሥነ ምግባሮች የጽድቅ ሥራዎች

ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚውሉ እግዚአብሔር ህልዎት አምለኮት መገለጫ የሚሆኑ የጽድቅ ሥራዎች ናቸው። ስለ እርሱ በቀጥታ የሚናገሩ፣ የሚሠሩ ለሱ።

ሀ/ እግዚአብሔርን መፍራት ለ/ ሃይማኖት ሐ/ ተስፋ መ/ ፍቅር
ሠ/ ቅድስና ረ/ ጸሎት ሰ/ ጾም ሸ/ ምፅዋት
ቀ/ ጽድቅ በ/ ንጽሕና

### ሰዎችን የሚመለከቱ የጽድቅ ሥራዎች

ሀ/ ጥበብ ለ/ አስተዋይ ሐ/ እውነተኛ መ/ ታማኝ
ሠ/ ንቁ ... ረ/ ጽኑእ ሰ/ ትዕግስተኛ ሸ/ ጨዋነት
ቀ/ ትህትና በ/ ሰላማዊነት ተ/ ልበ ሰፊ ቸ/ ህጻጊ በቀል
ነ/ ገር/ደግ/ ኘ/ ለጋስ አ/ ደስተኛ ከ/ አማኝ ወዘተ

## የሐጢአት ሥራ

ለእግዚአብሔር ሕግ በፈቃድ አለመገዛት በሃሳብም በንግግርም በሥራም ይህንን በመሳሰሉት ሁሉ አለመታዘዝን መግለጽ ነው።

ሥርዓት አልበኝነት ሕገወጥነት ልቅነት ማለት ነው።

የሥጋ ምኞት የሥጋም ፈቃድ ሁሉ ≠ጢአት ነው። ከእንስሳዊ ባሕሪይ የሚመነጭ የሚገታው የሚከለከለው የሌለ እንዲሁም የሚሠራ ነው።

የሥጋ ምኞት የሚባለውን ቅዱስ ጳውሎስ በገላ 5 ፣19-21 የገለጸውን ሲሆን ይህንም የማያደርግ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም። መመኘት የ≠ጢአት ሁሉ ሥር ናት። ስለዚህ እንደ ሰው ክፉ ምኞቱን ቶሎ ነቅሎ ካልጣለ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገች ሄዳ ወደ መሳምጀት ወደ መጓጓት ታደርሳለች። ቀጥሎ እንዲሠራት እንዲፈጽማት ትገፋፋለች።

ራስን ከልዩ ልዩ ልምድ ወይም አምሮት/ሱስ/ ማራቀና ራስን መቅጣት ስሜትን መሰብሰብና ሕዋሳትን በሙሉ ከክፉ ነገር መከልከል ይገባል። 1ኛ ዮሐ 2፣16።

ሰው በራሱ ላይ በመሞኘት ፈተናን ይጋብዛል እንጂ እግዚአብሔር ሰውን በክፉ አይፈተንም። ከዚህ በተጨማሪም ሰይጣን ራሱ ይፈታተነናል። መግቢያ ቀዳዳ በመፈለግ ሰውየው ሰንፎ በሩን ከፍቶ ካገኘው ያስነሣዋል። የእስም ተገዢና ፈቃዱንም ፈፃሚ ያደርገዋል። ሉቃ. 22፣31-32፣ የሐ.ሥ. 5፣3

በእርግጥ ምድራዊ ሕይወታችንን እንፈትን ዘንድ ግድ አለብን። ሆኖም ፈተናው ኃጢአት አይደለም። እንዲያውም የሚፈተነው ሁሉ ጻድቅ ነው። እግዚአብሔር በፈተናው ያጸናዋል እንጂ። እንዲያልፈውም ያስችለዋል። ያዕ. 1፣2-4

ለምሳሌ የትዕግስት አባት ኢዮብ ብዙ ፈተና ደርሶበት ሁሉን በትዕግስት አለፈው። ምርኃናም ዋጋም ተከፈለው። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በተለያየ መልክ በዲያቢሎስ ተፈተነ ነገር ግን ለፈቃዱ ስላልተገዛለት ድል አደረገው። እኛም ሦስቱ አርዕስተ ኃጣውእ ተብለው የሚጠሩትን ሦስቱን በትዕግስት፣ ፍቅረ ንዋይን በጸሊአ ንዋይ ትዕቢትን በትህትና ልናሸንፍ ይገባናል። ማቴ. 4፣14

ከሰይጣን ፈተና ለመውጣትና እሱንም ድል ለመንሳት ከብዙ መንገዶች ውስጥ፣

1.. እውነተኛ ጸሎት መጸለይ። «ወደፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ» በማለት ጌታ እንዳስተማረን። ሉቃ. 22፣4
2. ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመገዛት ሰይጣንን እንቢ ማለት ያዕ. 4፣7
3. ነቅቶ ተግቶና ታጥቆም ታጥቆም መኖር ነው። ዲያቢሎስ ይጥለን ዘንድ ዘወትር ይፈልጋልና። 1ኛ ጴጥ. 5፣8
4. ልማዳዊ ስሜታዊ ኃጢአትን ነቅቶ በቶሎ መሠረዝ ያስፈልጋል። ካልሆነ እንደ ሕጋዊ ሥራ እንዲቀጥል ያደርጋል።

## ኃጢአት

| | |
|---|---|
| 1. ኃጢአት ዘበጥንተአብሶ | 4. ኃጢአት ከባድ ሥርየት ያለው ስርየት የሌለው |
| 2. የግል ኃጢአት | 5. ቀላል ኃጢአት |
| 3. የጋራ ኃጢአት | 6. ከባድ ኃጢአት |

1. **ኃጢአት ዘበጥንተ አብሶ፡-** ከአዳምና ከሔዋን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ኃጢአት ነው፡፡ ከዘር ወደ ዘር ሲወርድ የመጣና የሰውን ዘር ሁሉ የበተነ ሲሆን በክርስቶስ ደም ተሽሯል፡፡
2. **የግል ኃጢአት፡-** ሰው በግሉ በራሱ የኀሊና ፈቃድ የሚሠራው ኀጢአት ነው፡፡
3. **የጋራ ኃጢአት፡-** በተመሳሳይ ጠባያቸው ተቀራርበው በመመካከር ይሁንብን ይደረግብን ብለው በጋራ የሚሠሩት ኃጢአት ነው፡፡
4. **ሥርየት ያለው ኃጢአትና ይቅርታ የሌለው ኃጢአት አለ፡-** የኸውም ሆኖ አንድ ኃጢአት የሚቀልበት ጊዜ /ምክንያት/ ይኖረዋል፡፡ በዚህ አንጻር የግል ኃጢአት በሁለት ይከፈላል፡፡

**ቀላል ኃጢአት፡** ኃጢአት መሆኑን ሳያውቁት ተገዶ ቀን ጥሎ ከዕውቀት ማነስና ከማስተዋል ጉድለት የተሠራ እንደሆነ በመጠኑ የቀለለ ይሆናል፡፡

**ከባድ ኃጢአት፡** ተጠንቅቀለት ቀን ተለይቶለት ውጤቱ ታውቆ ይሁንብኝ ይደረግብኝ ተብሎ የተሠራ እንደሆነ ከባድ ኃጢአት ይባላል፡፡

የከበደና የቀለለ ኃጢአት ለመኖሩ ጌታ በዮሐ. 19፣11 አስረድቷል፡፡ 1ኛ ዮሐ.5፣16 ማቴ. 12፣31 ኃጢአትን የማይሠራና ያልሠራ ከጌታና ከእናቱ በቀር ማንም የለም፡፡ ያዕ.3፣2 1ኛ ዮሐ. 1፣8፡፡ ኃጢአት ቀላል ነው እየተባለ ማድረግ ሳይሆን በየጊዜው እንደ ኃጢአትነቱ አውቆ መከላከልና ለመራቅ መሞከር የገባል፡፡ ካልሆነ ግን ወደ ከባድ ኃጢአት ያደርሳል፡፡ ለጊዜውም ቢሆን ኃጢአት ከእግዚአብሔር ፀጋ ያርቃል፡፡ ስለዚህ እውነተኛ ክርስቲያን ኃጢአትን ከሥሩ ቆርጦ መጣል በየጊዜው ንስሐ መግባት በእንባ መታጠብ ያስፈልጋል፡፡

## 1. ቀላል ኃጢአት የሚባሉት ከብዙ በጥቂቱ

| | | |
|---|---|---|
| መስረቅ | ኩራት | ክፋት |
| በቀለኝነት | ስስት | ነገረ ሰሪነት |
| ሐሜት | ስንፍና | |
| ክፉት መሥራት | ርኩሰት | |
| ደስኝታ ማጣት | ምቀኝነት ቅናት | |
| ተንኮለኛ መሆን | ስድብ፣ ተንኮለኝነት፣ ማቃለልና መሸንገል፡፡ | |

## 2. ከባድ ኃጢአት የሚባሉት

- መንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል መናገር
- አምልኮተ ጣኦት
- ክህደት
- ነፍስ ማጥፋት
- ዝሙት፣ አመንዝራነት፣ ሴሰኝነትና ግብረሰዶም፡፡

## ማጠቃለያ

«በሰማያት ያለው የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም፡፡» ማቴ. 7፣21፡፡ ይህ ቃል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው

ሰብከት መደምደሚያ ላይ የተናገረው ቃል ነው። ይኸውም ጌታንም አምነዋለሁ እያሉ በግብዝነት ጌታ ሆይ በማለት እግዚአብሔርን መሸንገል እንደማይቻል ያሳያል። ነገር ግን ጌታችንን የሚያምንና የሚወድ በከንፈር ሳይሆን በተግባር የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈጸም ፍቅሩንና እምነቱን መግለጥ አለበት።

ጌታችን ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገውን በአለት ላይ የተመሠረተ ቤት ሲመስል ቃሉን ሰምቶ የማያደርገውን ደግሞ በአሸዋ ላይ በተመሠረተ ቤት መስሎታል። ማቴ. 5፤24-27 በሌላ በኩል ደግሞ ሰምቶ የማይሠራውንና የማያደርገውን ሰው በመንገድ በጭንጫ እሾህ መሀል በተዘራ ዘር ስለመሰለው ቃሉን ሰምቶ የሚያደርገውን ደግሞ በመልካም በለምለም መሬት መስሎታል። ማቴ. 13፤1-23 እኛም በጎርፍ፣ በነፋስ፣ በዝናብ፣ ከተመሰለው መከራ ክህደትና ጥርጣሬ ተገፍተን ከመውደቃችን በፊት እምነትን በሥነ ምግባር አለትነት ላይ እንድንመሰርተው ካልሆነ ግን አወዳደቃችን ይከፋል። ልባችንን ገር የሕሊና ታዛዥ ብናደርገው በለም መሬት ላይ እንደተዘራው ዘር 30፣ 60፣ እና 100 መልካም ፍሬ እናፈራለን። ብዙዎቻችን መልካም ማድረግን ማለትም የእግዚአብሔርን በጎ ፈቃድ ለማድረግ እንፈልጋለን ነገር ግን እናደርገዋም የእግዚአብሔር ቃል «ለበጎ ፈቃድ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና ይለናል»፣ ፊል. 2፤13 ከዚህ የምንረዳው ሥነ ምግባር እግዚአብሔርን በማመን የሚገኝ መሆኑን ነው።

እግዚአብሔርን አምነን ሙሉ ሕይወታችንን በፊቱ ጥለን በልባችን ብናነግሠው ፈቃዱን ለማድረግ ያስተምረናል።

<u>ጥቅስ፤</u> «ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ» ያዕ. 1፤22

<u>ጸሎት፤</u> «አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ ቅዱስ መንፈስህንም በጽድቅህም ነፍሴን ከመከራዋ አውጣት» መዝ. 142፤10-11

### ወስብሐት ለእግዚአብሔር

## በመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት ትምህርት ክፍል ተዘጋጀ።


☎ 55 89 41

✉ 27314


፲፱፻፺፯ ዓ.ም.